# ኢትዮጵያዊነት

## ክፍል ፩

*ከቀመሩ ደሳለኝ*

ኢትዮጵያዊነት ማለት እጅግ ጥልቅ ረቂቅ ምስጢር፣ ልዩ መጠነ ሰፊ፣ ወሰን የሌለው የኢትዮጵያዊ የአገር ፍቅር መግለጫ ባህሪ ነው።

ኢትዮጵያንና በውስጧ ያሉ ሕዝቦቿን የያዘ ፍቅርና ትስስር፣ የማንነት፣ የዜግነት አለኝታ፣ የአገሪቱ ሉዓላዊነት፣ አገራዊ እምነት፣ የአንድነትና የኅብረት፣ የሰንደቅዓላማዋ አረንጓዴ -ቢጫ- ቀይ አርማና የነፃነት መግለጫ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ሉዓላዊነት ዳር ድንበር መከበር፣ ለሕዝቦችዋ እኩልነትና ደህንነት መጠበቅ ዋስትና መሆን ነው።

ኢትዮጵያዊነት ኑሮና ሕይወትን የሚነካ እምነት፣ ፍላጐትና ተስፋ የኅብረተሰብ ቅርስ ነው። ቅርስነቱ ለብዙ ሺ ዓመታት እየተወራረሰ የመጣ፣ የመከላከልና የማንነት መገለጫ፣ የመጠበቅ ዓላማ ቃል ኪዳን፣ ታማኝነትና የጀግንነት ፅናት ነው። ኢትዮጵያዊነት በኢትዮጵያ አገራዊ እምነት ላይ የተመሰረተ ጽኑ የመብት፣ የእምነት ነፃነታዊ ፍቅር ነው።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከጥንት ጀምሮ ተያይዘውና በአንድ ጠንካራ የታሪክ ሰንሰለት ተጋምደውና ተሳስረው በአንድነት የኖሩ የባለ ብዙ ቋንቋዎችና ባህሎች ሀገር መሆኗ የጥንካሬዋና የውበቷ መግለጫ የሕዝቧ ልዩ ቀለም የቀስተደመና መልኳ የታሪኳ አወንታ ነው።

ኢትዮጵያዊነት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰው የአስተዳደግ የቤተሰብና የአካባቢ ኅብረተሰብ ባህላዊ ጠባይ ማንነት፣ ምንነት፣ ምን የሚያደርግ የእኔነት ባህሪ ውጤት ነው። ሥርዓተ ማኅበር፣ ሥነ-ምግባር ያስተያየትና ያሰራር ልምድ የየዘመኑ ትውልድ ጽናትና ጥንካሬ የሚፈትኑ አያሌ ጥያቄዎችንና ችግሮችን እንዲሁም ከፊታቸው ለተደቀኑ ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ ሀሳቦችን ማቅረብና ማቀድ፣ የመወጣት ሃላፊነትና ተግባር የራሳችን የሚሉ ናቸው። ኢትዮጵያዊነት ከቤተሰብ እስከ ኅብረተሰባዊ ግንኙነት ባለው ምግባር የታነፀና የተቀረጸ ስሜት፣ እምነት፣ አስተሳሰብና መንፈስ በማንነት ታሪክ ላይ የበለጸገ አገርና እኔነት ነው።

ኢትዮጵያ በእያንዳንዱ ኅብረተሰብ እድገትና ኑሮ ውስጥ ባህላዊ ግንኙነት የተሳሰረ ለየትውልዱ የሚተላለፍ የአኗኗር ሥርዓት አለው። ኢትዮጵያዊ ባህሉ ተመሳሳይነት፣ ተዛማጅነትና ተወራራሽነት ያለው አንድ ወጥነቱን ያስመሰክራል። በኢትዮጵያ የግዛት

አንድነት ውስጥ በሁሉም አካባቢ ባህሉ ያደረገው ምግባር፣ ደግነት፣ትህትና፣ ቁምነገረኝነት፣ መልካም እንግዳ ተቀባይነትና ሰው አክባሪነት በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው።

ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ የተለያዩ የኑሮ መሰረት ያላቸው ሁሉን አንድ የሚያደርግ ወግና ባህል መፈቃቀድና መከባበር፣ መተሳሰብና አክብሮትን ያቀፉ ኅብረተሰቦች አገር ናት።

ይህ ኅብረተሰብ ከ7 ሺህ ዓመታት በላይ አብሮና በጋራ ችግርና ደስታን በአንድነት ተካፍሎ ቆይቷል። ሕዝቦቿ በጋብቻ ተሳስረው እየተጋቡ፣ እየተደበላለቁና እየተዛመዱ የሚኖሩ፣ ባህላቸውም የተወራረሰና የተደባለቀ፣ በእምነት የተቆራኘ፣ አስተዋይና ጀግና፣ አንድ ብሔራዊ ሕዝብ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ሥር በኢትዮጵያዊነት ፀንቶ፣ የአንድ ታሪክ ባለቤት ዘላለማዊ ፍቅርና ነፃነት ያለው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነው። ኢትዮጵያዊነት አንድነት፣ በእጅጉ ተከባብሮ የሚኖር ኅብረተሰብ ዋና መለዮ መጠሪዋ ነው።

ኢትዮጵያዊ ለሚያደርገው ሁሉ ጥንቁቅና አርቆ አሳቢ፣ ይሉኝታን ምግባሩ ያደረገ ከብዙ ነገሮች ቁጥብና ውስን የረጋ ነው። ከመናገር ማዳመጥን የሚመርጥ ባህላዊ እሴት አለው። ለዚህም አገላለጽ “መናገር ብር ነው ዝምታ ግን ወርቅ ነው” ይሉታል። ይህ ሃቅ ነው የኢትዮጵያዊነት ትግሥት መግለጫ ነው ዝምተኝነት ብልህነትን ታጋሽነትን የሚገልጽ ጭምት ባህሪው ነው።

ኢትዮጵያዊነት ንግግርና አነጋገርን ፣ ሀሳብንና አስተያየትን አዛምዶና አወራርሶ የሚናገር፣ የሚሰራውን የሚያውቅ፣ በእምነቱ የሚጸና ነው። እውነት፣ ሃቅ፣ ቆራጥ፣ ፅናት፣ ልበ- ሙልነት፣ አሞተ- ከስታራ፣ ወኔ-ሙሉነት፣ አደርገዋለሁ-ባይነት ላቀደውና ለአመነው በፍጹም ፅናት ለግብ የሚበቃ ኢትዮጵያዊነት ባህሪ ነው።

ኢትዮጵያዊነት አትንኩኝ ባይነትን፣ አልደፈርም ማለትን፣ ገበናን መሸፈን፣ ይሉኝታና መጠራጠርን ይህንና የዚህ መሰል ጠባዮች የሁሉም ኅብረተሰብ ኢትዮጵያዊ ባህሪዎች ናቸው።

ኢትዮጵያዊነት ቁጥብ፣ ታላቅንና አንጋፋን ማክበር ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ነው። ጥንካሬንና ፅናትን፣ ፍቅርንና ደስታን፣ ቅሬታንና ሐዘን፣ እምነትንና ተስፋን ከፈጣሪው ጋር በአለው ግንኙነት የኑሮውንና የሕይወቱን ወሳኝነት በእምነቱ ላይ አጉልብቶ በሁሉም ኅብረተሰብ የሚንጸባረቅ ኢትዮጵያዊ ባህሪ አለው።

በታሪካችንና በባህላችን መሰረት ኢትዮጵያዊነት ማለት (ሳይንቲስት ኢንጅነር ቅጣው እጅጉ ጠቅለል አድርጎ እንዳስቀመጠው)

- ቅንና እውነተኛ
- ሃይማኖተኛ/ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው
- ጥበብን በልቡ ያሳደረ
- ትውልድን አክባሪ
- አስተሳሰቡ ጤነኛ
- አገር ወዳድና ጀግና
- ጠንካራና ብርቱ
- ዳፋር
- አትንኩኝ ባይ
- ሲጠቃ አሻፈረኝ ባይ ነፃነት አፍቃሪ ነው።

ተስፋን እየተመገቡ በቆራጥነት፣ በፅናት መከራን መቻል የሁሉም ኢትዮጵያዊ መለኪያ ፀባይ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ተስፋ የማይቆርጥ፣ ብርቱና ታጋይ እራስን ከፍ በማድረግ ለቆመለት ዓላማ በቁርጠኝነት ከግብ የሚያደርስ ነው። ኢትዮጵያዊነት ኅብረተሰባዊ አካል ነው። ኢትዮጵያዊነት ኀጠኝነትን የሚቃወም የሰው ልጅ ክብርና እኩልነትን ከፍ አድርጐ በቀደምትነት የሚያይና ለዚያ ነፃነትና መብት በአጠቃላይ ለኢትዮጵያዊ ምንነት የቆመ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ጨዋነት፣ መተሳሳሰብና መፈቃቀድ አስተዋይነት፣ አርቆ አሳቢነትና ሚዛናዊነት ባህሪ ያለው ሰፊ ምዕራፍ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ክብርና ኩራት፣ መመኪያና መኩሪያ አለኝታ ብዙ ጀግኖች በየትውልዱ የተሰውላት፣ የኢትዮጵያ ስቃይና መከራ፣ የሐዘንና ደስታ ስሜት ነው። ኢትዮጵያዊነት አሻፈረኝና እምቢ ባይነት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ፍቅርና ነፃነት ነው።
- ኢትዮጵያዊነት እውነትና ሃቅ ነው።
- ኢትዮጵያዊነት ቆራጥነትና ፅናት ነው።
- ኢትዮጵያዊነት ጀግንነትና ደፋርነት የአርበኝነት ባህሪ ነው።
- ኢትዮጵያዊነት ጥንካሬና ብርታት ነው።
- ኢትዮጵያዊነት የአገር ዋስትና ግዴታና ኃላፊነት ነው።

*ኢትዮጵያዊነት አይዋሽም፣ ኢትዮጵያዊነት አይክድም ኢትዮጵያዊነት ውሸትና ክህደትን መቋቋም፣ ባንዳና ሴረኛ ማጋለጥና ማውደም፣ ነቃቅሎና ፈንግሎ መጣል ነው።*

*ኢትዮጵያዊነት በአገሩ ዳር ድንበር፣ ቅርስና ሃብት አይደራደርም፣ አይሸጣትም ይሞትላታል እንጂ ኢትዮጵያዊነት ለእናት አገሩ ፈጥኖ ደራሽ ልጆቹ የምትላቸው ጠባቂ አለኝታ ነው። ኢትዮጵያዊነት በአገሩ ጉዳይ፣ በአገሩ በደል ተቆጭ፣ ተናዳጅ እልከኛ፣ ሳያወላውል ፈጥኖ ተባባሪና እየተደራጀ በየአውራው መሪነት የሚከትና የማያዳግም ጀብዱ የሚሰራ ነው። ኢትዮጵያዊነት የነጠረና የጠለለ፣ የማይዘቅጥ ትውልድ አትራፊ ነው። ኢትዮጵያዊነት ከምንም ከማንም በላይ ሰፊ የማይበገር የነፃነትና የአንድነት ትስስር የክብርና ኩራት አርማ ነው።*

***ኢትዮጵያዊነት ሕያው ነው !***